ቀን፡ ታህሳስ 24 /2003 ዓ.ም

**በውጭ ሃገር ለምትገኙ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች፣**

**ለሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ**

**<u>በያላችሁበት</u>**

እኛ የመኢአድ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ፓርቲያችን አሁን ያለበት ሁኔታ በእጅጉ ከሚያሳስብ ደረጃ ላይ መድረሱን ተገንዝበናል፡፡ ፓርቲውን በማዳንም ሆነ ጉዳቱን አስከፊ በማድረግ እንደ ወሳኝ ጉዳይ የሚቆጠረው የጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ ሊሆን እንደሚችል ትንቢት መሰል መልዕክት ከጉባዔው በፊት አስተላልፈን ነበር፡፡ እንደተባለውም ፓርቲው ከነታሪኩ ሊጠፋ ታሪካዊ የተንኮል ተልዕኮ ካላቸው ግለሰቦች ጋር ተፋጧል፡፡ ይህንን አስደንጋጭ፣ አሳዛኝና አሳፋሪ የታሪክ ጅምር ባፋጣኝ ለመግታት የመኢአድ የታሪክ ደም ያለባችሁ ሁሉ ሳታመነቱ እንድትነሱ ባለፉት ዓመታት የተሰውት የመኢአድ ሰማዕታት ደም ይጠራችኋል፡፡

ግንቦት 15/2002 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ ማግስት የተገኙ ውጤቶችና የተከሰቱ ችግሮች የሚገመገሙበት፣ ጠንካራ ጎኖች ተፈትሸው የሚቀጥሉበት፣ የታዩ ድክመቶችና ያጋጠሙ ችግሮችም ውይይት ተካሂዶባቸው የመፍትሄ እርምጃ የሚወሰድባቸውና በአዲስ ኃይል ለአዲስ ትግል ዝግጅት የሚደረግበት ወቅት እንደነበረ ግልጽ ነው፡፡

በ2002 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ በተቃዋሚ ኃይሎች ላይ በገዥው ፓርቲ የደረሰው አሳዛኝ ድርጊት በአንዳንድ ፓርቲዎች ሲገመገምና አቋም ሲወሰድበት መኢአድ የምርጫውን ውጤት እንደተቀበለ በሚያስመስል ሁኔታ የአመራር አካሉ አባላቱን በትኖ፣ ውይይት ከማካሄድና የአቋም መግለጫ ከማውጣት ይልቅ በሩን ዘግቶ አባላቱ በጉዳዩ እንዳይነጋገሩና እንዳይጠያየቁ አደረገ፡፡ ይባስ ብሎ ፕሬዚዳንቱ በድንገት ሥልጣኔን ለቅቄያለሁ ማለታቸው በአባላቱ መካከል ድንጋጤና ሃዘንን ፈጠረ፡፡

አባላቱ በጽ/ቤታቸው ግቢ በመገናኘት ስለአጠቃላዩ ሁኔታ ምክክርና ውይይት ሲጀምሩ አመራሩ «ሳትጠሩ አትምጡ፤ አትመላለሱ፤... » በማለት በግቢው እንዳይገኙ በመከልከል በደረሰባቸው ቁስል ላይ መርዝ ተነሰነሰበት፡፡

በዚህ ወቅት የፓርቲው አጠቃላይ ሂደት ያሳሰባቸውና በምርጫውም ውጤት እልህ የያዛቸው ተቆርቋሪ አባላት ዝምታውን ለመስበርና ጠንካራ አቋም መያዝ እንዲቻል ለመመካከር ተጠራርተው ተሰባሰቡ፡፡

የፓርቲው ዝምታ፣ የአባላቱ በወቅቱ አለመሰባሰብ፣ የሕዝባችንም የነፃነትና የዲሞክራሲ ተስፋ መጨለም መሪዎቻችንን ይቀስቅሳቸውና ለትግል ያዘጋጁን እንደሆነ በማለት ለክብራቸው በሚመጥን አገላለጽ «አሰባስቡን፣ አወያዩን፣ ታሪክ የጣለባችሁን አደራ ተወጡ » በማለት ሰኔ 23 ቀን 2002 ዓ.ም የአቤቱታ ማሳሰቢያ ጽፈን ለፕሬዚዳንቱ በአድራሻቸው ላክን፡፡

አመራሮቻችን አሰባስቡን፣ ለትግል አዘጋጁን ተብለው ቢጠየቁ ከሥራ አስፈጻሚ እስከ ታችኛው አባል ድረስ የተወሰኑትን በጽሑፍ በማገድ፣ ሌሎችን በማባረር፣ አንዳንዶቹን ደግሞ ለሥራዎቻቸው እንቅፋት እየሆኑ በማስመረር ከፓርቲው እንዲርቁና የመሳሰሉትን አስከፊ ድርጊቶች በመፈጸም ከስድስት የማይበልጡ ግለሰቦች በሥራ አስፈጻሚነት ሥም ፓርቲውን ይዘው ተቀመጡ፡፡

ሁኔታው እጅግ ያሳሰባቸው ተቆርቋሪ አባላት÷

1, የታገዱ አባላትን በማሰባሰብ፣

2, የተባረሩ አባላትን በመጥራት፣

3, በቅሬታ የተገለሉትን በመመለስ እና

4, የፓርቲውን ትንሳዔ የሚፈልጉ አባላትን ሁሉ በማቀናጀት <u>**የመኢአድ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ**</u> አቋቋሙ፡፡ ትግሉ መሠረታዊ ለውጥ በሚያሳይ ሁኔታ እንዲካሄድ አደረጃጀቱን በአዲስ አበባና በክልሎች ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደረገ፡፡ እውጭ ሃገር ከሚገኙ ኢትዮጵያውያንም ጋር በተለያዩ ጊዜያት የስልክና የኢሜል ልውውጦች ተካሄዱ፡፡

ከ2002ቱ አገር አቀፍ ምርጫ ውጤት መገለጽ በኋላ ሥራቸውን አቋርጠው የነበሩት የፓርቲው ፕሬዚዳንት ወደ ጽ/ቤት እንዲመለሱና አባላቱን አረጋግተው ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሂደት የሚተካቸውን መሪ እንዲያስመርጡና ፓርቲውን ለብልሽትና ለብዙ ጥፋት የዳረጉትን ግለሰቦች እንዲያስነሱና በሌሎች ጠንካራ አባላት እንዲያስተኩ ለማድረግ ሰፊ ጥረት ተደረገ፡፡

ፓርቲው መሠረታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ለማድረግ በእኛ በኩል የሚደረገው ጥረት ብቻውን በቂ እንደማይሆን በመረዳት በውጭ ሃገር ያሉ የኢትዮጵያ ጉዳይ የሚያገባቸው፣ የመኢአድ አደጋ ውስጥ መሆን በቀጥታ የሚመለከታቸውና ኃላፊነት የሚሰማቸው ሁሉ ፕሬዚዳንቱን ከማግባባት አልፎ ግፊትና ጫና እንዲያደርጉ አሳሰብን፡፡ በዚህ ወገናዊ ጥሪ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ሌሎችም ፓርቲውን ለማዳን ብርቱ ጥረት አድርገዋል፡፡ ለዚህም ጥረታቸው ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን፡፡

በእኛ ትግልና በውጭ ሃገር በሚገኙ ደጋፊዎች ጥረት የመኢአድ ጠቅላላ ጉባዔ ተጠርቷል፡፡ በጠቅላላ ጉባዔው ላይ ከደንብ ውጭ በህገ ወጥነት የተፈጸሙ ተግባራት መኖራቸውን ተገንዝበናል፡፡ እነዚህም፦

1ኛ, በ2000 ዓ.ም በነበረው ጠቅላላ ጉባኤ የተሣተፉ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በሙሉ በተለያዩ ምክንያቶች ከጐደሉት በስተቀር የአሁኑ ጉባኤ ተሣታፊ መሆን ነበረባቸው፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ አካባቢ በጠቅላላ ጉባዔ አባልነታቸው መገኘት ይገባቸው የነበሩ ሰዎች በአሁኑ ጉባዔ እንዳይገኙ የተደረጉበት ሁኔታ አለ፤ በእነሱ ምትክ ግን የመኢአድ አመራሮች ለሚቀጥለው ህገ ወጥ እንቅስቃሴያቸው እንዲያመቻቸው የእነሱን ዓላማ ለማራመድ ሊያግዙን ይችላሉ ያሏቸውን ከየቦታው በማሰባሰብ እንዲሳተፉ አድርገዋል፡፡

2ኛ. የተጓደለ የሥራ አስፈፃሚ አባል ቢኖር የተጓደለውን የሥራ አስፈፃሚ ማሟላት የሚችለው ቢቻል ጠቅላላ ጉባኤው ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ጠቅላላ ጉባኤው መሰብሰብ ካልቻለ ደግሞ የላዕላይ ም/ቤቱ ተሰብስቦ በተጓዳሉት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በመተካት ቃለ ጉባኤ ይዞ በየደረጃው ለሚመለከታቸው አካላትና ለምርጫ ቦርድ ጭምር ያሣውቃል፡፡ የ2002ቱ ጠቅላላ ጉባዔ ተስማምቶባቸው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል እንዲሆኑ ካደረጋቸው መካከል አብዛኞቹ ተጓድለው አምስት ብቻ ሲቀሩ ማሙያ የተካሄደው በፕሬዚዳንቱና በጥቂቶቹ አመራሮች መልካም ፈቃድ ነበር እንጂ በላዕላይ ምክር ቤቱ ስብሰባ አልነበረም፡፡

በዚህ ህገወጥ አሠራር የላዕላይ ም/ቤት አባል ሣይሆኑ ከላይ በተጠቀሱት ሰዎች ብቻ ስለተወደዱ የሥራ አስፈፃሚ ሆነው ተመድበው እየሰሩ የነበሩትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለምሣሌ፦ ያህል **አቶ ያቆብ ልኬ (እኚህ ግለሰብ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል በሆኑበት ወቅት እንኳን የላዕላይ ምክር ቤት አባል ሊሆኑ ይቅሩና የፓርቲውም አባል አልነበሩም፡፡** ፓርቲው ባሰራሩ አንድ ሰው በአዲስነቱ ሙሉ አባል ከመሆኑ በፊት ለተወሰኑ ጊዜያት በእጩ አባልነት መቆየት እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ይህ ህግ ተጥሶ ቀጥታ አባል ያውም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡) አቶ ብርሃኑ ወ/ሰንበት፣ አቶ አብርሃም ጌጡ፣ አቶ አክሊሉ ንህነና የመሣመሉት ይገኙበታል፡፡

በሌላ በኩል የላዕላይ ም/ቤት አባል ሆነው ግን የላዕላይ ም/ቤቱ ሣያውቅና ሣይፈቅድ  በኢንጂነር ኃይሉ ሻወልና በመሰሎቻቸው በግል ስለተወደዱ ብቻ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሆነው በህገወጥ መንገድ እንዲገቡ የተደረጉም አሉ፡፡ ለምሳሌም ያህል  ወ/ሮ መሠሉ ረዳ ፣ አቶ አዳሙ ተሰማና የመሣሠሉት ይገኙበታል፡፡ ጠቅላላ ጉባዔውን ያዘጋጀው ይህ በህገ ወጥ መልኩ ሰዎች የተሟሉለት ሥራ አስፈፃሚ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

3ኛ, የ2000 ዓ.ም ጠቅላላ ጉባኤ ሲጠናቀቅ ከተስማማባቸው ጉዳዮች አንዱ የላዕላይ ም/ቤት አባላት በየአራት (4) ወራት እንዲሰበሰብና የፓርቲውን ወሣኝ ሥራዎች ሁሉ መስራት፣ ውሣኔዎች እንዲያሳልፍ እና የዕለት ከዕለት ሥራዎች ደግሞ በሥራ አስፋፃሚው እንዲከናወኑ መመሪያ እንዲሰጥ ኃላፊነት የመስጠት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በጠቅላላ ጉባዔው የተመረጡት 105 የላዕላይ ም/ቤት አባላት ባለፉት ሁለት ዓመት ከመንፈቅ ጊዜ ውስጥ አንድ ጊዜም ስብሰባ እንዲያካሂዱ አልተደረገም፡፡ ም/ቤቱ እንኳን ተሰብስቦ ውሣኔ ሊሰጥ ይቅርና አባላት እርስ በርሣቸው በወጉ የመተዋወቅ ዕድል አላገኙም፡፡ ይኽ አካል ነበር ለዚህ ጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ ብዙ ዕቅዶችን ማውጣትና መመሪያዎችንም መስጠት የነበረበት፡፡ ነገር ግን ላዕላይ ም/ቤቱ ፍጹም እንደሌለ ተቆጥሮ ከህግ ውጭ አመራር ላይ በተቀመጡ ግለሰቦች የፓርቲው ውሳኔ ሲተላለፍ ቆየ፡፡  እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ነው  በህገ ወጥ መንገድ የተቀመጠው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ የጠራው፡፡

4ኛ, የተወሰኑ የሥራ አስፈፃሚና የላዕላይ ም/ቤት አባላት እንዲሁም የወጣት አመራሮች ፓርቲው ከውድቀት እንዲድን እርምት ይወሰድ እያሉ የአመራሮችን የስህተት መንገድ ስለሚያጋልጡና ጠንክረውም የፓርቲውን ሥራ ስለሚሠሩ ጠቅላላ ጉባዔው ላይ እንዳይሳተፉ ተከልክለዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፣

1. ወ/ሪት መሶበወርቅ ቅጣው፣ የመኢአድ ህዝብ ግንኙነት ኮሚቴ ኃላፊ የነበሩ፣
2. አቶ ጌታቸው አበበ፣ የሥራ አስፈፃሚና የምርጫ ጉዳይ ኃላፊ የነበሩ፣
3. አቶ ተስፋዬ ፋንታ፣ የላዕላይ ም/ቤት አባልና የጉለሌ ክ/ከተማ ተጠሪ፣
4. ኮሎኔል ትርሲት ገ/መስቀል፣ የላዕላይ ም/ቤት አባልና የቦሌ ክ/ከተማ ተጠሪ፣
5. አቶ ነብዩ ከንፈ፣ የአንድነት ጋዜጣ ም/ዋና አዘጋጅና የላዕላይ ም/ቤት አባል፣
6. አቶ ጌታነህ፣ ዓለም የላዕላይ ም/ቤት አባል አደራጅና የሰሜን ቀጠና አስተባባሪ፣
7. አቶ ከበደ ታዬ፣ የላዕላይ ም/ቤት አባል አድራጅና የምዕራብ ቀጠና አስተባባሪ
8. ወጣት ኃይለ ገብርኤል ታምራት፣ የአዲስ አበባ ወጣቶች ምክር ቤት ሰብሳቢ እና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

5ኛ, የታገዱ ሰዎች አጠፉ ቢባል እንኳን በደንቡ መሠረት አመራሩ በመጀመሪያ የቃል፣ቀጥሎ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ነው ጊዜያዊ እገዳ ሊያደርግ ይገባ የነበረው፡፡ እገዳው ሊጸናም ሊሻር የሚችለው ባለጉዳዮቹ በጠቅላላ ጉባዔው ፊት ቀርበው ውይይት ከተደረገበት በኋላ እንጂ አሁን አምባ ገነኖቹ እንዳደረጉት የእልክና የጭፍን እርምጃ ሊወሰድባቸው አይገባም ነበር፡፡

6ኛ, ጉባዔው ከመከፈቱ ጥቂጥ ቀደም ብለን ወደ ጉበዔው እንድንገባ ስብሰባው የተካሄደበት በር ላይ ቆመን ኢንጂነር ኃይሉን «ልናነጋግርዎት እንፈልጋለን» ብንላቸውም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ ስብሰባው አዳራሽ አጠገብ ሔደን ሰው ልከን በተወካይ እንዲያነጋግሩን ብንጠይቅም ያገኘነው ምላሽ ግቢውን በፍጥነት ካለቀቃችሁ በፌደራል ፖሊስ ትባረራላችሁ የሚል ነበር፡፡

6ኛ, ጉባዔው ከተከፈተ በኋላ በጠቅላላ ጉባዔው ላይ ስብሰባ እንዳይገቡ የተከለከሉ ሰዎች ከውጭ ቆመዋልና እንዲገቡ ይደረጉ፤ እያሉ የተለያዩ ሰዎች አስተያየት ቢሰጡም ሰሚ ስላላገኙ ሳንገባና ጉዳያችን ሳይታይ ስብሰባው ቀጥሏል፡፡

7ኛ, በጉባዔው ላይ የውጭ ኦዲተር ያልመረመረው የፋይናንስ ሪፖርት በአቶ ማሙሸት አማረ በኩል ቀረበ፡፡

8ኛ, በፓርቲው አሰራር ውስጥ ቁጥጥር አለመኖሩ የፈጠረው የአሠራር ብልሽት በኦዲትና ኢንስፔክሽን ተመርምሮ ሪፖርት ለጉባዔው አባላት አልቀረበም፡፡

9ኛ, በጠቅላላ ጉባዔው ላይ ፓርቲያችንን እያደሙት ያሉት የአመራር አባላት በሁለት ጎራ ተከፍለው እርስ በርስ በመናቆር ጉባዔውን በማወካቸው ያሉትን ፕሬዚዳንት በአዲስ ሊተካ ተዘጋጅቶ የነበረው ጉባዔ የሁኔታዎችን አስከፊነት በመረዳቱ ለተወሰነ ጊዜ ነባሩ ፕሬዚዳንት በሃላፊነት እንዲቆዩ አደረገ፡፡ ነገር ግን ከጥንቱም ፍላጎታቸው የቀዘቀዘው ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ዲሞክራሲን ገድለው፣ የጉባዔውን መንፈስ በመቀየር ይጠበቅ የነበረውን መሠረታዊ ለውጥ በመቃረን እነዚያኑ «መኢአድን ያፈርሳሉ» ተብለው የሚፈሩትን ሰዎች በከፍተኛ አመራር ላይ እራሳቸው ሾሟቸው፡፡

አመራሮቹ ጉባዔውን እንዲጓዝ ከፈለጉበት መንፈስና ውጤት እንዲሁም ፕሬዚዳንቱ ከደረሱበት መደምደሚያ መረዳት የሚቻለው የኢትዮጵያና የሕዝባችን ችግሮች ከደማቸው ያልተዋሃደና ከልባቸው ያልሰረፀ በመሆኑ ፀፀት የማይሰማቸው መሆኑን ነው፡፡

10ኛ, ከጠቅላላ ጉባዔውም በኋላ እነዚህ በድጋሚ በሥራ አስፈጻሚ ወንበር እንዲቀመጡ የተደረጉ ሰዎች አሁንም ጎራ ለይቶ የመጣላቱን ጉዳይ ከቀድሞው በከረረ መልኩ እያባባሱት ይገኛሉ፡፡ ያለመግባባታቸው ደረጃ ከቃላት መዘላለፍ አልፎ እጅግ አስጊ ደረጃ በመሸጋገሩም የመኢአድ ጽ/ቤት በፖሊስ ተከቦ ስብሰባ እስከማካሄድም ተደርሷል፡፡ ታዲያ በዚህ ሁኔታ ነወይ መኢአድ የሚመራው? እንዴትስ ነው የተነሳበትን ትግል የሚያካሂደው?

የእነዚህ ያሳዘኝ ድርጊቶች ውጤት መጨረሻቸው ከሚከተሉት ሦስት አማራጮች አንዱን ለማከናወን መሆኑን ያመላክታል፡፡

1, በተቃዋሚ ሥም መኢአድ የገዥው ፓርቲ አጫፋሪ ሆኖ በደካማነት እንዲቀጥል ማድረግ፣

2, በህብረብሔራዊነት እየተጓዘ ያለውን መኢአድ በውህደት ሥም ባልተጠናና ጥንቃቄ ባልተሞላበት ሁኔታ በብሔር እተደራጁ ፓርቲዎች ጎራ ውስጥ በመክተት የፓርቲውን አባላት፣ ንብረትና ሃብትን ለሌሎች መጠቀሚያ አሳልፎ መስጠት፣

3, ሰነድ ቀዶ፣ ታሪክ አጥፍቶ፣ አባላቱን በመበተን ህልውናውን ማሳጣት፣

መኢአድ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ሰላማዊ ፓርቲዎች ሁሉ በታሪኩ የሚመስለው የሌለ ልዩ ፓርቲ ነው፡፡ የተመሠረተው ሰላማዊ ሰዎች ከነነፍሳቸው ገደል በሚጣሉበት፣ በሳንጃ በሚታረዱበት፣ ከተወለዱበት፣ ካደጉበትና ከአረጁበት መንደር በሚፈናቀሉበት፣ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከባድ ሰቆቃ በተፈጸመበት ወቅት ነበር፡፡ ይህንን አሳዛኝና ከባድ ሰቆቃ ለመቀልበስ በተደረገው ጥረት ብዙ የደም መስዋዕትነት ተከፍሏል፡፡ ይህን በልዩ መስዋዕትነት የተመሰረተ ፓርቲ የመጠበቅ አደራ በሁላችንም ትከሻ ላይ አርፏል፡፡

አሁን የመኢአድ ፓርቲን እየመራ ያለው ቡድን በተቀነባበረ ልዩ ስልት የተዘጋጀ ስለሆነ ተልዕኮውን ከላይ ከተጠቀሱት ሦስት አማራጮች አንዱን ማስፈጸም እንደሆነ ከእያንዳንዱ እንቅስቃሴው መገንዘብ ተችሏል፡፡

አባሎቻችን የከፈሉት መስዋዕትነት ከንቱ ሲቀር፣ ከህዝቡ ጋር ያስተሳሰረን አኩሪ ታሪክ ሲደመሰስና ሲጠፋ፣ ህዝባችንም መቋጫ ለሌው ችግር ሲዳረግ ዝም ብለን ማየት አንችልም፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት የጥፋት መንገዶች እንዲቋረጡ፣ አንድነታችን እንዲጠበቅና ኃይላችን እንዲጠናከር በብቃት መደራጀት አስፈላጊ መሆኑ በሁላችንም ዘንድ የታመነ ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት ማን ምን እንደሚሰራ ግልጽ የሥራ ክፍፍል

በማድረግ መላ አባላቱን በአጭር ጊዜ ለድል በሚያበቃ ሁኔታ ተጠናክረን በሚከተለው ሁኔታ መዋቅራችንን ዘርግተን **መኢአድን ለማዳን** ወደ ሥራ ገብተናል፡፡

በዚሁ መሠረት፣

1, ሰብሳቢ ወ/ት መሶበወርቅ ቅጣው

2, ም/ሰብሳቢ አቶ ተስፋዬ ፋንታ

3, ጸሐፊ አቶ ፀጋዬ ግዛው

4, የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ጌታነህ ዓለም

5, የቅስቀሳና ፕሮፖጋንዳ ኃላፊ አቶ ጌታቸው አበበ

6, የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ አቶ ነቢዩ ከንፈ

7, የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ አቶ ማርቆስ ገብሬ

8, የንብረት ጉዳይ ኃላፊ አቶ አቅናው ሰርፀወልድ

9, የማኅበራዊ ጉዳይ ኃላፊ ኮሌኔል ትርሲት ገብረ መስቀል

10, የሕግና ዲሲፕሊን ጉዳይ ኃላፊ ሻለቃ ጣሰው ሽፈራው

11, የአዲስ አበባ አስተባባሪ አቶ ረታ ቤተማርያም

12, የክልሎች አስተባባሪ አቶ ከበደ ገድሉ

13, ኦዲትና ኢንስፔክሽን ኃላፊ መቶ አለቃ ዓለማየሁ ዘለቀ

14, የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ ወጣት ኃይለገብርኤል ታምራት

በዚህ አደረጃጀት መኢአድ በመሠረታዊ ለውጥ እስኪታደስ ድረስ በጊዜያዊነት ተዋቅረን የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ሁሉ በመክፈል በጥንካሬና በብልሃት ትግሉን ለመቀጠል ወስነናል፡፡

ሃገር ሲደፈርና ወገን ሲነዳ በአፋጣኝ ተሰባስቦ በአንድነት የመቆም አኩሪ ታሪክ ያለን ኢትዮጵያውያን፣ ዛሬም መኢአድን ከአፈጠጠበት አደጋ ለመታደግ የዕውቀት፣ የጉልበት፣ የገንዘብና የማቴሪያል አቅማችንን በማቀናጀት በአንድነት እንድንቆም ታሪክ እየጠራን ነው፡፡

***ሃገሬ፣ ወገኔ፣ ዜጋዬ የምትሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ! መኢአድን ለማዳን በሚደረገው በዚህ ወሣኝ ትግል ጥበብ በተሞላበት ዕውቀታችሁ እና በአለ ኃይላችሁ ሁሉ ከጎናችን በመቆም አብራችሁን እንድትሠሩ በታላቅ አክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡***

የመኢአድ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ

**መኢአድን ከነታሪኩ እናስከብረዋለን!!!**

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!**

**አንዲት ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!**